# ፍቅርና ሰላም

በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች የሚታተም ወርሃዊ ጋዜጣ


A Monthly Amharic/English Newspaper Published by the Catholic Bishops' Conference of Ethiopia (CBCE) General Secretariat/ECS

# LINK

ቁጥር 572 | ታህሳስ 2017 ዓ.ም | ዋጋው የኢት. 15.00 ብር




# እንኳን ለጌታችን ለመድኀኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓል በሰላም አደረሰን!



## የኢትዮጵያ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ሊቀጳጳሳት ብፁዕ ካርዲናል አቡነ ብርሃነየሱስ የ2017 ዓ/ም የጌታችን የመድኀኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን የልደት በዓል በማስመልከት ለመላው ምዕመናን ያስተላለፉት መልዕክት

ወደ ገፅ 3

## 57ኛው የኢትዮጵያ ካቶሊክ ጳጳሳት መደበኛ ጉባኤ ተካሄደ

ወደ ገፅ 2

## የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ሰበካዊ የምክክር ጉባኤ አካሄደ

ወደ ገፅ 6

## “ነገር ግን እንደ ሰው ሆኖ በመወለድ የባርያን መልክ ይዞ ራሱን ባዶ አደረገ " ፊል 2፡ 7

በክቡር አባ ዳንኤል አሰፋ

ገፅ 6

## ኢዮቤልዩ እና የቤተሰብ ጸሎት

በክቡር አቶ አርጋው ፋንቱ

ገፅ 5

## በመንፈሳዊነትና በእምነት ማደግ

በክቡር አባ አብነት አበበ

ገፅ 4

## “ገናን ለምንድን ነው የምናከብረው?”

በክቡር ካቲኪስት ወርቁ ጦጤ

ገፅ 4

የብፁዕ ካርዲናል አቡነ ብርሃነየሱስ የ25ተኛ የጵጵስና የብሩራዊ ኢዮቤልዩ ዓመትን በማስመልከት ሥጦታ ለማቅረብ ለሚፈልጉ ሁሉ የቁሳዊ ሥጦታ ቀርቶ የትምሕረት ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ወጣቶች እንደሚውል በማሰብ ካርዲናል አቡነ ብርሃነየሱስ የሚል የገንዘብ ድጋፍ ዕድል መመቻቸቱን ገልጸው በተዘጋጀው የባንክ አካውንት መላው ካቶሊካውያን እና በጎ ፍቃድ ያላቸው ሁሉ ለዚህ በጎ አድራጎት ድጋፍ እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል።

**Cardinal Berhaneyesus Fund**

Account Name: **Cardinal Berhaneyesus Fund**
Account Number: **1000523294338**
Commercial Bank of Ethiopia, Mahatema Gandhi Branch
Swift Code: **CBETETAA**

# ፍቅርና ሰላም

መስከረም 1967 ዓ. ም. ተጀመረ

አሳታሚ ቤተ ሊቀ ጳጳሳት ዘካቶሊካውያን

በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት የማኅበራዊ መገናኛና ሕዝብ ግንኙነት ማስተባበሪያ በየወሩ ተዘጋጅቶ የሚወጣ መንፈሳዊ ጋዜጣ



ዋና አዘጋጅ | አባ አበራ ማኬቦ
ምክትል ዋና አዘጋጅ | አቤል ሙሴ
ማኔጂንግ ኤዲተር | ቤዛዊት አሰፋ
ተቀዳሚ ረዳት አዘጋጅና ሪፖርተር/ኤዲተር | ገብሩ ሃ/ዮሐንስ
ምክትል ረዳት አዘጋጅ | መሳይ ማሪዮ
ፐሩፍ ሪደር | የምሥራች አሰፋ
ሌይ አውት 1 | ጨረቃ ዘውዴ
ሌይ አውት 2 | ቤተልሔም ታደሰ
ስርጭት | ማኅበራዊ መገናኛና ሕዝብ ግንኙነት ማስተባበሪያ


ፖ. ሣ. ቁ. 2454 አዲስ አበባ ስልክ - (0111) 55 03 00 ፋክስ (0111) 55 31 13 E-Mail - scpr@eccsdco.org Website - https//www.cbce-gs.org

# ርዕሰ አንቀጽ

## የምሥራቹ ቃል ዛሬም ይሰማ



እነሆ ለእናንተና ለሕዝቡ ሁሉ ደስታ የሚሆን ታላቅ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ። እነሆ ዛሬ በዳዊት ከተማ መድህን ተወልወዶላችኋል። ይህም ብሩክ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው (ሉቃ 2፡-12። ምሥራቹን የሚነግሩን ቅዱሳን መላዕክት ናቸው። ቅዱሳን መላዕክት በብርሃን እየኖሩ የእግዚአብሔርን ብርሃን አበሩ ፣ በቃላቸውም "በሰማይ ለእግዚአብሔር ክብር በምድርም በጎ ፈቃድ ሆነ ( ሉቃ 2፡13) በማለት የምሕረትን ዓመት አወጁልን።

የቅዱሳን መላዕክት ምስጋናና ዝማሬ፤ የእረኞች የተነገራቸው ቃል ሳይጠራጠሩ ማየታቸውና መደሰታቸው፣ የቅድስት ድንግል ማርያም በልቧ ውስጥ አምቃ የያዘችው ፀጋ፣ የምድር ፍጥረታት ደስታ የእግዚአብሔር ፍቅርና ምሕረትን በጊዜና በቦታ እንደማይገደብ እኛም እንመሰክራለን።

እግዚአብሔር ዓለምን እጅግ ስለወደደ አንድ ልጁን ሰጠ። ስለዚህ በልጁ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት ይኖረዋል እንጂ አይጠፋም (ዮሐ 3፡-16)። ቀድሞ በእግዚአብሔር ዘንድ በቃል መልክ የነበረው ሥጋ ለብሶ ከሰማያት ሰማያት ወርዶ ራሱን ዝቅ በማድረግ ወደ ሰዎች እንዲመጣ የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆነ። ይህ የሆነበት ዋናው መነሻና ምክንያት ደግሞ እግዚአብሔር ለሰዎች ያለው ፍቅር ነው። እግዚአብሔር ዓለምን እጅግ ስለወደደ በሰው አእምሮ መረዳት የሚያዳግተውን መለኮታዊ ምሥጢር ለሰዎች ገለጠ። ይህም የዓለም ብርሃን፣ የሕይወት እንጀራ፣ መንገድና እውነት፤ ፍቅርና ሰላም የሆነው ልጁን ላከ። እግዚአብሔር የዓለም ፈጣሪ የሆነው ትልቁ ጌታ እንዴት የትንሹን ሰው መልክ መስሎ የሰው ሥጋ ለብሶ ሰው ሆኖ በመገለጥ ማደሪያውን በሰዎች መካከል አደረገ የሚለው ምሥጢር ድንቅ ነው። እግዚአብሔር በፍቅር ስለ ፍቅር ብዙዎችን ወደ ፍቅር መንገድ ለመምራት ብሎ አደረገው። እርሱ ዝቅ ያለው እርሱ የተዋረደው ብዙዎች ወደ ላይ ከፍ እንዲሉ፣ ብዙዎች እንዲከበሩ ነው። እርሱ ሕይወቱን የሰጠው ብዙዎች ዘላለማዊ ሕይወት እንዲያገኙ ነው። በእኛ መካከል ሥጋ ለብሶ ያደረው ጌታችን መድኃኒታችን እየሱስ ለክርስቶስ ዛሬም እድናየውና እንድናውቀው ይጠራናል። በማቴዎስ ወንጌል "ንጹሕ ልብ ያላቸው እግዚአብሔርን ስለሚያዩ ደስ ይበላቸው" (ማቴ 5 ፡-8) ይላል። የልብ ንጽሕና ማለት የእግዚአብሔርን ጸጋ የተላበሰ ሕይወት ማለት ነው። የልብ ንጽሕናቸውን ጠብቀው ለመኖር የሚጣጣሩ ሰዎች በዕለታዊ ሕይወታቸው ውስጥ ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ ግንኙነት መስርተው ይኖራሉ። በልባቸው ውስጥ በሚያድረው የእግዚአብሔር መንፈስ አማካይነት በውስጣዊ ልቦናቸው እግዚአብሔርን ያያሉ። እነርሱ በሁሉም ነገር እግዚአብሔርን ያስቀድማሉ፤ በመንፈስ ከእርሱ ጋር ይወያያሉ የእርሱን ፈቃድ እየጠየቁ ሕይወታቸውን ይመራሉ። ከዓመተ ዓለም ወደ ዓመተ ምሕረት ያስገባን ራሱ እግዚአብሔር ነው። እኛም የዕድሉ ተጠቃሚ እንድንሆን ሁልጊዜ ያገኘነውን የበራልንን ብርሃን እንከተል አንልቀቅ።

እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር 2025 ዓ.ም. ላይ ደርሰናል። ዘመኑን በክርስቶስ ያገኘነውን ብርሃን ደግመን ደጋግመን እንድናሰላስለው ራሳችንን ወደ ውስጥ እንድንመለከት ቤተክርስቲያን እንደ ሁልጊዜው ጥሪ አድርጋልናለች። ምሕረት ተቀባዮች ብቻ ሳይሆን ምሕረት አድራጊዎች እንዲሁም ይቅር ባዮችና ይቅርታ አድራጊዎች መሆን መታደል ነው። ቤተክርስቲያን የኢየቤልዩ ዘመን ስታውጅ ሰላምን በብቸኝነት የሚሰጠን ክርስቶስን በልባችንና ደግመን ደጋግመን በመኮትኮት መልካም ፍሬ አፍርተን ለተተኪያችን ማስተላለፍን አንርሳ።

የክርስቶስን የልደት ቀን(ገና) ምክንያት አውቀውትም ሆነ ሳያውቁ በመላው ዓለም ይከበራል። ልዩነቱ ጊዜያዊውን ደስታ ተሻግሮ የማየት ጸጋ ካልተሰጠን እና ለማግኘት ጥረት ካላደረግን የክርስቶስ ልደት ትርጉሙን በቀላሉ መረዳት ቀላል አይደለም። ዘላለማዊ ደስታ የሚሰጠን አንድና አንድ ክርስቶስ ብቻ ነው። በዘመኑ ትንሽ የነበረችውና ዛሬ የዓለም መሰባሰቢያ እንደሆነችው ቤተልሔም መንደር ከፍ አድርገን የእግዚአብሔርን ምሕረት እናውጅ።

**እንኳን ለብርሃነ ልደቱ አደረሳችሁ።**



**የፍቅርና ሰላም ጋዜጣ ኤዲቶሪያል ቦርድ**

※※※

**ለመላው ካቶሊካውያን እና በጎ ፍቃድ ያላቸው ወገኖች ሁሉ እንኳን ለጌታችን ለመድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓል በሰላም አደረሳችሁ**

※※※

**በማለት ምኞቱን ይገልጻል። እግዚአብሔር ሀገራችን ኢትዮጵያን ይባርክ!!!**

## 57ኛው የኢትዮጵያ...

ከገፅ 1 የዞረ

የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ብጹዓን ጳጳሳት 57ኛው መደበኛ ጉባኤያቸውን ሞጆ በሚገኘው የሱባኤ ማዕከል ከህዳር 30 እስከ ታህሣስ 4 ቀን 2017 ዓ.ም. አካሄዱ።

ጉባኤው በርካታ የቤተክርስቲያን አጀንዳዎችን በመያዝ የተካሄደ ሲሆን በዋነኝነት በቫቲካን ሲካሄድ የቆየውን የመጨረሻው ዙር የሲኖዶስ ውይይት ውጤት አፈጻጸም፣ የሀገራችን ወቅታዊ የጸጥታ እና የኢኮኖሚ ሁኔታ፣ የወጣቶች እና የካህናት ህይወት፣ የምዕመናን ህንጸት እና ሐዋርያዊ ሥራዎች ላይ፣ ሥርዓተ ሉጡርጊያ እና የቤተክርስቲያን ህጋዊ ሰውነት በሚመለከት በሰፊው መወያየታቸው ተገልጿል።

ጉባኤው በእነዚህ አንኳር ሀሳቦች ላይ ለተከተታይ 4 ቀናት ሲወያይ መቆየቱን ብፁዕ አቡነ ልሳነክርስቶስ የባህርዳር ደሴ ሀገረስብከት ጳጳስ እና የጳጳሳት ጉባኤ ቃል አቀባይ የገለጹ ሲሆን የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በተለይም ሁለት ሳምባዎች በሆኑት ላቲናውያን እና ግዕዛውያን ሥርዓተ ሉጡርጊያው የተዋቀረች በመሆኗ ሥርዓቱ ጸሎትነቱን እንደጠበቀ እንዲካሄድ እና ማስተካከያ የሚያስፈልጋቸው ሁኔታዎች ላይ ለእርማት የሚያግዙ የተልዕኮ አቅጣጫዎች እና አጋዥ የሚሆኑ ውሳኔዎችም መተላለፋቸውን ገልጸዋል።

የጳጳሳት ጉባኤው በማጠቃለያው ላይ ወቅታዊ የሀገራችንን የጸጥታ እና የኑሮ ሁኔታ በማስመልከት ሐዋርያዊ መልዕክት አስተላልፈዋል። በመልዕክታቸውም በስብከተ ገና የዝግጅት ወቅት በአገራችን በጦርነት፣ በውስጥ ግጭቶች፣ በኢኮኖሚ የዋጋ ንረት ሳቢያ በጭንቀት እና በአስከፊ ሁኔታ ላይ የሚገኙትን ማሰብ እንደሚገባ ገልጸዋል። "በዚህ የስብከተ ገና ወቅት የአዳኛችንን ልደት ለማክበር መዘጋጀት ብቻ ሳይሆን ራሳችንን እውነተኛ የሰላም መሳሪያ ለመሆን እናዘጋጅ። ጥላቻ እና መከፋፈልን በክርስቶስ ፍቅር የሚያሸንፍ፣ ተስፋ የቆረጠውን በክርስቶስ እውነተኛ ተስፋ የሚሞላ ማህበረሰብ ይኖረን ዘንድ ሁላችንም ልባችንን ክፍት ልናደርግ ይገባል።" ብለዋል። በተጨማሪም መሪዎች፣ የኃይማኖት አባቶች፣ ፖለቲከኞች፣ የኢኮኖሚ ባለሙያዎች እና መላው ማህበረሰብ ለውይይት፣ ለፍትህ እና ለሰላም እንዲቆምም ጥሪ አቅርበዋል።

**"ሕፃን ተወልዶልናልና፥ ወንድ ልጅ ተሰጥቶናል፤ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል። ስሙም ድንቅ መካር፥ ኃያል አምላክ፥ የዘላለም አባት፥ የሰላም ልዑል ይባላል።" ኢሳ.9:5**

# የኢትዮጵያ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ሊቀጳጳሳት ብፁዕ ካርዲናል አቡነ ብርሃነየሱስ የ2017 ዓ/ም የጌታችን የመድኀኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን የልደት በዓል በማስመልከት ለመላው ምዕመናን ያስተላለፉት መልዕክት

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ፡ አሜን!

## “ነገር ግን የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ” (ወደ ገላትያ ሰዎች 4፤4)



*በክርስቶስ የተወደዳችሁ ብፁዓን ጳጳሳት*
*ክብራን ካህናት፣ገዳማውያንና/ውያት*
*መላው ምዕመናንና የአገራችን ሕዝቦች*
*በመላው ዓለም የምትኖሩ*
*ኢትዮጵያውያንና*
*ትውልደ ኢትዮጵያውያን ወገኖች በሙሉ*

የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን የልደት በዓል ለማክበር የተዘጋጃችሁ ምዕመናንና የእግዚአብሔር ቤተሰቦች እንኳን ለ2017 ዓ.ም. የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓል በሰላም አደረሳችሁ። ይህንንም የልደት በዓል ምክንያት በማድረግ ይህን መንፈሳዊ መልዕክት ሳስተላልፍላችሁ እስከዚች ዕለትና ሰዓት በደህና አድርሶን የልደት በዓልን ለማክበር ላበቃን አምላክ ምስጋና በማቅረብ ነው።

በየዓመቱ የልደት በዓልን እናከብራለን የጌታ ልደት ከሌሎች ልደቶች ይለያል። እንደምናውቀው የታላላቅ ሰዎችን ልደቶች ማክበር የተለመደ ነገር ነው። ለአንድ አካባቢ ሕዝብ ወይንም ለሰው ልጆች በሙሉ አንድ ቁምነገር ያበረከተ ሰው ይከበራል። በዚህም ክርስቶስ ምን አደረገ? ምን አስተማረ? ምን አመጣ? ብለን ልንጠይቅ ይገባል።

እንዲህ ዓይነት ጥያቄዎች ማቅረብ የልደትን በዓል ትልቅነት እንድናስተውል ያደርገናል። የልደትንበዓልስናከብር፤የጌታንልደት፤የጌታን ጥምቀት፤ የጌታን ስብከቶች፤የጌታን ታምራት፤ የጌታን ሕማማቱን፤ ሞትና ትንሣኤውን እያሰብን ሊሆን ይገባል።

የዛሬ በዓላችን ከቤተክርስቲያን ውጭም በቤተሰብም፣ በማኅበራችንም ሊንጸባረቅ ይገባል። በወንጌል ፈሪሳውያን በአብዛኛው የክርስቶስን ትምሕረት ሲቃወሙ እናያለን። ከዚህ ምን እንማራለን? እንደ እነርሱ የምንሆንበት አጋጣሚዎች አሉ ወይ ብለን ሕይወታችንን እንመርምር። “እንደ ሕፃናት ካልሆናችሁ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት አትገቡም” (ማቴ.18፡3) የሚለውን የጌታ ልደት ነው የምናከብረው። ሕጻናት በወላጆች ወይንም በአሳዳጊዎች ሥር ጥገኛ እንደሆኑ ሁሉ እኛም በእግዚአብሔር ሥር ጥገኛ መሆናችንን ስናውቅና ስንገነዘብ የክርስቶስ የልደት በዓል ይደምቃል። ልባችንን ያበራዋል ለደስታችን ሙላት ይሰጠዋል። ትልቅ ትርጉምም ይኖረዋል።

የዛሬ ሁለት ሺህ ዓመት ሐዋርያት የዕለት ኑሮ ሥራቸውን ትተው ክርስቶስን ተከተሉ፣ በእርሱም ተማረኩ። የገና ልደት እንግዲህ የሚያምረው በእኛም ዕለታዊ ሕይወታችን ውስጥ ክርስቶስ ምን ያህል ቦታ አለው ብለን ስንጠይቅ የደመቀ በዓል ይሆናል። ከበዓላችን ወደ ሕይወታችን፤ ከሕይወታችን ደግሞ ወደ በዓላችን በልባችን መመላለስ ያስፈልገናልና ነው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሲሞት ከሮም የተላከ የመቶ አለቃ “በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ነበረ“ (ማቴ.27፡54) ብሎ መሰከረ። የልደት በዓል የእግዚአብሔር ልጅ የልደት በዓል መሆኑን እንድናስተውል ዕድል ሰጠን። በዚህም የክርስቶስ ልደት ከዝነኞች ሰዎች ልደት በላይ መሆኑን ያሳየናል። በአጭሩ ክርስቶስ ደስ የሚለውን ለማወቅና ለመፈጸም ስንፈልግ ነው የገና በዓል በልባችንና በማኅበራችን የሚደምቀው።

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በዘመን የማይወሰን ሆኖ በዘመናችን ውስጥ መጣ። የዘመን ባለቤትና የዘመን ፈጣሪ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ገባ። እኛ ግን እንደ ሰው ያለፈውን እናስታውሳለን። የሚመጣውን እንጠብቃለን፤ ካለፈው ዘመን ወይንም ካለፉት ጊዜያት የሚያበሳጩን ነገሮች ይኖራሉ። የሚቆጩንም ነገሮች ይኖራሉ። እንደዚሁም የሚመጣው ዘመን ያስፈራን አሊያም ያስጠነቅቀን ይሆናል። በእነዚህ ጊዜያት የሚያጽናናን ዛሬ ልደቱን የምናከብረው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፤ ምክንያቱም ያለፈውን ከቁጭት የሚያድነው ቁስልንም የሚፈውሰው እርሱ ነውና። እንደዚሁም የወደፊቱን አስመልክቶ ከስጋት የሚታደገን ዛሬ ልደቱን የምናከብረው ጌታ ነው። ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ሮሜ ሰዎች በጻፈው መልዕክቱ ”በዚህ ተስፋ ድነናል” ይላል (ሮሜ 8፤24)። የሚያድነንና የሚያጽናናን በበረት የተወለደው ሕፃኑ ኢየሱስ ነው። በመልኩና በአርዓያው የፈጠረውን ሰው ሊጎበኝና ሊያድን የመጣው ወልደ አምላክ ነው።

በዘመናችን የሰው ልጅ ያለእግዚአብሔር ብዙ ነገሮችን መፈፀም የሚችል ይመስለዋል። ነገር ግን ከዚሁም የተነሣ በጨለምተኝነትና በአፍራሽ ሐሳቦች ይዋጣል። የሕይወትን ትርጉም ያጣል። ያጣውንም ሰላም በማይሆኑ ጊዜያዊ ነገሮች ለመተካት ይሞክራል፣ የሥነ ምግባርን ዋጋ ይስታል፣ የማጋራትን ፀጋ ይነፍጋል፣ ከሰው ክብር ይልቅ ሥልጣንን፤ ክብርንና ምቾትን ይፈልጋል። ነገር ግን ምንም ቢያገኝ በመጠን መኖር ያቅተዋል። በቃኝ ማለትን ይረሳል። ለተራበውና ለተጎሳቆለው ወንድሙና እህቱ ማዘን ይሳነዋል። በእግዚአብሔር መልክና አምሳያ የተፈጠረው ወንድሙና እህቱ አያሳዝኑትም፤ ዳሩ ግን ያለ እምነት ያለ ተስፋና ፍቅር እሩቅ መሄድ አይቻልም። ለእግዚአብሔር ቦታ የማይሰጥ ግለሰብ ወይንም ማኅበረሰብ ለተስፋም ቦታ መስጠት አይችልም። የሰው ልጆች ፍልስፍና ገደብ አለው፤ እነርሱም በእግዚአብሔር ሲባረኩ ከእግዚአብሔር ሲመነጩ ግን እሩቅ ያደርሳሉ።

የሰው ልጅ የተፈጠረው ለእውነተኛ ደስታና ለዘለዓለማዊ ሕይወት ነው። የገና በዓልም የዚህ ምሥራች ነው። የደስታ ምንጭ ጌታ ደስታን ሊያበሥረን ብቸኝነታችንን ሊያጠፋ ተወለደ። ጨለማችንን የሚገፍ ብርሃን ተወለደ፣ አለማወቃችንን የሚሽር ጥበብ ተወለደ። ከራስ ወዳድነት የሚያድን ጌታ ሕይወትን ሊለግሰን ተወለደ። ፍርሃታችንን ሊያስወግድ አማኑኤል ተወለደልን። እንዲህ ዓይነቱ የምስራች ቤተሰቦቻችንን እንዲያጽናና በርና መስኮቶቻችንን እንክፈት። ይህንን የምስራች በልባችን ጓዳ ውስጥ እናስቀምጥ። የዘወትር የልባችን ሃብትና መዝገብ ይሁንልን። እንዲህ ከሆነ የጌታ ልደት የሕይወታችንን አቅጣጫ ይመራዋል።

የተከበራችሁ ምዕመናን ይህ የልደት በዓል እምነታችን የሚጎለብትበት፤ ለፍትሕ የምንቆረቆርበት፤ ለተቸገሩ የምናዝንበት እንዲሆን እንፀልይ። ይህ የልደት በዓል ወደ እግዚአብሔር የምንቀርብበት ይሁንልን።እውነተኛ ደስታ ከእግዚአብሔር የሚገኝ ደስታ መሆኑን የምናስተውልበት ይሁን። የነቢዩ ኢሳያስ ትንቢት ሁልጊዜ በልባችን ውስጥ ይመላለስ።

”ሕፃን ተወልዶልናል ወንድ ልጅም ተሰጥቶናል አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል ስሙም ድንቅ መካር ኃያል አምላክ የዘለዓለም አባት የሰላም ልዑል ይባላል ለመንግስቱም ስፋት ለሰላሙም ብዛት ፍጻሜ የለውም ከአሁን ጀምሮ እስከ ዘለዓለም መንግስቱን በፍትሕና በጽድቅ ይመሠርታል። ደግፎ በመያዝም ያፀናዋል። በዳዊት ዙፋን ይቀመጣል አገሩንም ሁሉ ይገዛል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር የዘላለም አባት ቅናት ይህን ያደርጋል” (ኢሳ.9.5-6) ይህ የነቢዩ ኢሳይያስ መልዕክት በአንክሮ ሊታይ ይገባዋል። የልደት በዓል እራሳችንን እንድንጠይቅ ሊያግዘን ይገባል። የሰው ልጅ በእውቀት በቴክኖሎጂ በሌሎችም ነገሮች ማደጉ በራሱ ክፋት የለውም ጥያቄው ግን በሥነ ምግባር እና በመልካምነት ምን ያህል አደገ የሚለው ነው የሰው ልጅ ከጦርነት፤ ከጥላቻ፤ ከቅናት፤ ከግፍና ከሐሰት ምን ያህል ተላቀቀ ብሎ መጠየቅ ያሻል። ካልሆነ ግን በእውነት አደገ እንዴት ማለት ይቻላል? የሰው ልጅ እራሱን እንዳልፈጠረ ሁሉ እራሱን ለማወቅ በዙርያው ያለውን ማጥናት አይበቃውም፤ ይልቁንም እራሱን ሊመረምር ይገባዋል፤ የሰው ልጅ ከሚገኝበት አሳዛኝ ሁኔታ ከገባበት ገደል፣ ከተዘፈቀበት ማጥ፣ የሚያወጣው የልደት ባለቤት የሕይወት ምንጭ የሆነው ክርስቶስ ነው። የሱንም ልደት ስናከብር ይህንን እያስተዋልን ይሁን። ከተወለደው ሕፃን ጋር በመሆን የሰው ልጅ ማደግ ይችላል ምክንያቱም የሰው ልጅ ብቻውን ቢጥር ሊፈጽመው የማይችለውን እንዲችል የሚያስችለው ጌታ መምጣቱን የሚገነዘብበት በዓል ነው።

መድኃኒታችን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደበት ጊዜ ”ሰላም በምድር” የሚል የምሥራች ዜና በምድር ላይ መሰማቱ የሰላምን አስፈላጊነት በበለጠ አጉልቶታል። ሆኖም የሰው ልጅ በዓለም ላይ በሰላም መኖር የሚችለው ሰላም ሊፈጠር የሚችልበትን የፍትሕና ርትዕ ተግባር በመፈፀም እንጂ በኃይልና በግዴታ ብቻ አይደለም። በዚህ ዓለም ላይ ሌላውን እንደራስ ከማየትና አንድ ሰው በራሱ ላይ ሲደረግ የማይፈቅደውን ነገር በሌላ ላይ ለማድረግ ካለመፍቀድ የተሻለ የሰላም ጎዳና አይኖርም። ስለዚህ ለሰላም ኑሮ መሠረት የሆነው ይህ ፍትሕና ርትዕ በአገራችና ላይ ይሰፍን ዘንድ የቤተክርስቲያናችን የዘወትር ምኞትና ፀሎት ነው።

በእግዚአብሔር ፊት ሁሉም እኩል እንደመሆኑ መጠን በዚህች ለምለም ምድር ላይ ሰውን ያኖረው በሰላምና በደስታ እንዲኖር ነውና። የክፋትና የጥላቻ ተልዕኮ ከአገራችን ጠፍቶ አገራችን ትባረክልን ዘንድ ቤተክርስቲያን ዘወትር ትፀልያለች። ስለሆነም ከአገራችን መከራና ችግር ሐዘንና ሰቆቃ ጦርነትና ስደት ተወግዶ በሕዝቦቻችን መካከል ሰላምና ፍቅር እንዲሰፍንልን የሰላም አምላክ ለአገራችን ሰላሙን ፍቅሩንና አንድነቱን ይስጥልን።

በመጨረሻም በዓሉ በመተሳሰብና በመረዳዳት የምናልፍበት፤ የታመሙት የሚድኑበት፤በጭንቀትና በመከራ ላይ የሚገኙትን እግዚአብሔር ሰላምንና መረጋጋትን እንዲሰጣቸው ፤ከአገራቸውና ከቄያቸው ርቀው በስደት ላይ ያሉትን እንዲያጽናናልን፤ በየማረሚያ ቤቶች ያሉትን እግዚአብሔር እንዲያስባቸው፣ ያዘኑትን እነዲያጽናናቸው፣ ወላጆቻቸውን ያጡትን ልጆች እነዲያበረታታልን፣ የሞቱትን በመንግስቱ እንዲቀበላቸው እየተመኘን በዓሉን የሰላምና የደስታ በዓል ያድርግልን። የሰላም ንጉስ የሆነው ሕፃን ኢየሱስ ለአገራችንና ለዓለሙ ሁሉ ሰላሙን ይስጥልን።


መልካም የልደት በዓል ለሁላችሁም ይሁንላችሁ።

† ብፁዕ ካርዲናል አቡነ ብርሃነኢየሱስ
ሊቀጳጳሳት ዘካቶሊካውያን

**"ቃልም ሥጋ ሆነ፤ በእኛም ዘንድ አደረ፤ ጸጋንና እውነትን የተሞላውን ፥ የአባቱ አንድያ ልጅ በአባቱ ዘንድ ያለውን ክብሩንም አየን።" ዮሐ.1:14**

# በመንፈሳዊነትና በእምነት ማደግ

**‹‹ኢየሱስም በጥበብና በቁመት በሞገስም በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ያድግ ነበር›› (ሉቃ. 2፥52)**



በክቡር አባ አብነት አበበ
ዘማኅበረ ልኡካን/ ላዛሪስት

የሰው ልጅ ይወለዳል ያድጋል ያረጃል ይሞታል፤ ይህ የተፈጥሮ ሂደት ነው። በዚህ ሂደት ውስጥ የልደታችንን ቀን ስናከብር ተጨማሪ እድሜ የሰጠንን አምላክ እያመሰገንን እድገታችንን ስናየው ለካስ እድሜዬ እየሄደ ነው እንላለን። ይህም አካላዊ እድገታችንን የምንለካበት (ለውጣችንን የምናይበት) ሲሆን መንፈሳዊ እድገታችንም የምንለካበት መንገድ አለ።

### የመንፈሳዊነታችን መለኪያው

እድገት በአካል ብቻ ሳይሆን በመንፈሳዊነትና በእምነት የሚታይ ከሆነ መቼ ነው በእምነትና በመንፈሳዊነት አድገናል ተለውጠናል የምንለው? በመንፈሳዊነት ስንጠነክርና ስንደክም መለኪያው ምንድን ነው? መንፈሳዊ ሕይወታችን ሲታመምና ሲሞት የምናውቀው እንዴት ነው? እንዴትስ ነው መንፈሳዊ ሕይወታችንና እምነታችን ሊያድግ የሚችለው? ለምላሹ አንድ ወዳጄ የላከልኝና ከፌስቡክ ገጽ ላይ ተለጥፎ ያገኘሁትን በማጣመር እንደሚከተለው አቀረብኩት።

መንፈሳዊ ሕይወት በአንድ ቦታ ላይ የቆመ ነገር ሳይሆን የሚያድግ ነው። ሰው በእድሜው ወይም በአካል ትልቅ ስለሆነ በመንፈሳዊነትም ትልቅ ነው (አድጓል) አይባልም ምክንያቱም መንፈሳዊ ሕይወት በእድሜና በቁመት አይለካምና።

አንድ ሰው ልክ እንደ ኒቆዲሞስ መንፈሳዊ መሪ (የኃይማኖት አባት) ሊሆን ይችላል ነገር ግን መንፈሳዊ ጉዳዮችን በተመለከተ መንፈሳዊ ነገሮችን የማወቅና የመረዳት ሁኔታው አናሳ ሊሆን ይችላል (ዮሐ. 3፥1-20)። ከዚህም ባሻገር በመንፈሳዊነት አለመብሰል በሌላም መንገድ ይገለጻል።

ለምሳሌ በስልጣናቸውና በእድሜአቸው እውቀታቸው ተጨምሮበት አንቱ የተባሉ መንፈሳዊ ሰዎች ለእኔ ወገኖች ብቻ ሲሉ ስናይ፣ለሰዎች (በተለይ ለምስኪኖች) የማይሆን ተስፋ ሲሰጡና ቃላቸውን ሲያጥፉ (ሲዋሹ)፡ እንዲሁም እነርሱን የማይመጥን ነገር ሲያደርጉ ቢገጥመን ልንደናገጥና ልንፈርድባቸው እንችል ይሆናል፤ በሰዎች ላይ መፍረድም በመንፈሳዊነት ያለማደግ ምልክት እንደሆነ ልብ ይሏል። አንድ የክርስቶስ ተከታይ የሆነ በቤተክርስቲያን ትልቅ ቦታ ያለው ግለሰብ በአስተሳሰቡ በአነጋገሩና በድርጊቱ ከደረጃው ዝቅ ብሎ ብናገኘው ልንሰናከል አይገባም በመንፈሳዊነት ያለመብሰል ጉዳይ ነውና እንጸልይለት።

### የፍቅር መኖር (መንፈሳዊ ጥንካሬ)

ለእግዚአብሔር እና ለባልንጀራችን ጠንካራ ፍቅር ሲኖረን መንፈሳዊ ህይወታችን ጠንካራ የመሆኑ ማሳያ ነው (ማቴ. 22፥36-40)

### የፍቅር መቀዝቀዝ (መንፈሳዊ ድካም)

ለእግዚአብሔርና ለባልንጀራ የምንሰጠው ፍቅር አናሳ ከሆነ በመንፈሳዊነት ደካሞች የመሆናችን ምልክት ነው (1ዮሐ. 4፥20)

### በመንፈሳዊነት የመታመም ምልክት

ከእግዚአብሔር ይልቅ ሌላ ነገር ስንወድ (ለምሳሌ፡- ገንዘብ ስልጣን ጎሳ ዘር...ወዘተ..) ወይም ከእርሱ በላይ የምንወደው ሲኖር ነው በመንፈሳዊ ሕይወታችን ታመናል የሚባለው። (ማር.10፥21-31)።

### በመንፈሳዊነት የመሞት ምልክት

አንድ ሰው በመንፈሳዊ ሕይወቱ ሞቷል የሚባለው በኃጢአት ውስጥ ተዘፍቆ በሚኖርበት ጊዜ ነው (1ዮሐ. 5፥7)። አንዳንድ ጊዜ በመንፈሳዊ ህይወታችን ከጠንካራነት ወደ ደካማነት፣ ከመታመም ወደ መሞት የምንወርድበት ጊዜ አለ። በሌላ ጊዜ ደግሞ በተቃራኒው ከሞተ መንፈሳዊነት ወደ ታመመው፣ ከደከመ መንፈሳዊነት ወደ ጠንካራ መንፈሳዊነት ከፍ የምንልበት ጊዜ አለ። እንግዲህ መንፈሳዊ ሕይወት የከፍታ እና የዝቅታ ጊዜ ካለው መቼ ነው በመንፈሳዊ ሕይወቴ መሻሻሌንና አለመሻሻሌን (ማደግ አለማደጌን) የማውቀው ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው።

### ጾም ምጽዋትና ጸሎት ለመንፈሳዊ እድገት

ጸሎት፣ ጾም እና ምጽዋት በጣም ጥሩ ነገሮች ናቸው ነገር ግን መንፈሳዊ እድገት አሳየን የምንለው በምናደርገው የጸሎትና የጾም ብዛት ወይም የልገሳ ብዛት ሳይሆን ለእግዚአብሔርና ለባልንጀራችን ባለን የፍቅር መጠን ነው። ስለዚህ ልገሳዎቻችን ጸሎቶቻችና ጾማችን ለእግዚአብሔርና ለባልንጀራችን ያለንን ፍቅር እንድናሳድግ የሚያግዙን ሊሆኑ ይገባል። በመሆኑም መንፈሳዊ እድገታችንን ለመለካት ለእግዚአብሔርና ለባልንጀራችን ያለን ፍቅር አድጓል ወይስ አላደገም የሚለውን መመልከት በቂ ነው።

## በመንፈሳዊነትና በእምነት ለማደግ ምን እናድርግ?

አካላዊ እድገታችን ከእግዚአብሔር ባሻገር የብዙ ሰዎች እገዛና የብዙ ነገሮች ጥምረት እንዳለበት ሁሉ ለመንፈሳዊ እድገታችንም እግዚአብሔር ሰዎችና ሌሎች ነገሮች ያስፈልጉናል። ከእነኚህ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ይገኙበታል።

በመንፈሳዊ ጉዞ የሚያግዙን የነፍስ አባት መኖር፣ ሱባኤ መግባት፣ ጥሩ ወዳጅ/ጓደኛ፣ በየእለቱ የሕሊና ምርመራ ማድረግ፣ መጽሐፍ ቅዱስንና መንፈሳዊ መጽሐፍትን ማንበብ፣ በመንፈሳዊነት የሚያንጹ ስብከቶችን ማዳመጥ፣ የጸሎት ጊዜ የሰዎችን ስሜት ለመረዳት መጣር፣ እንደስጦታችን ማገልገል፣ ትኩረታችንን በእግዚአብሔርና በመልካም ስነ ምግባሮች ላይ ማድረግ፣ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር መተባበር፣ ከውስጥም ሆነ ከውጭ ከእግዚአብሔር ጋር ከሚያለያዩን ነገሮችም ሆኑ ሰዎች መለየት (መራቅ)።

### ኃጢአትን መናዘዝ

በእምነታችንና በመንፈሳዊነታችን ለማደግ ልክ እንደ ቅዱሳን ኃጢአታችንን ለካህን መናዘዝና በምስጢረ ንስሐ እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ዘላለማዊ ፍቅር መገንዘብ ያሻል። በንስሐ የኃጢአት ጨለማ ከእኛ ይወገዳል፣ ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት ይታደሳል።

### የመቁጠሪያ ጸሎት ማድረስ

ማርያም እናታችን ናት። በህይወት ውጣ ውረድ ውስጥ ስናልፍ, እርሷ ከእኛ ጋር ትጓዛለች. የመቁጠሪያ ጸሎት ስናደርግ የክርስቶስን ሕይወት በማርያም ውስጥ በጥልቀት እንመለከታለን፤በእርሷ አማላጅነት ልጇን ክርስቶስን ስንጠይቅ እንደ ደቀ መዛሙርቱ በታማኝነት እንድንከተለው የሚያስፈልገንን ጸጋ ይሰጠናል።

### ኢየሱስን መጎብኘት

በቅዱስ ቁርባን ከሚገኘው ኢየሱስ ጋር በየቀኑ ቢያንስ ለ15 ደቂቃ አብሮ መሆን ጊዜአችንን የሚያባክን ሳይሆን ከእሱ ጋር ያለንን ግንኙነት የሚያሳድግ ነው።

### መስዋእተ ቅዳሴ

በክርስቲያናዊ አምልኮ ውስጥ ዋናው ነገር መስዋእተ ቅዳሴን በመሳተፍ በማሰብ በመናገር በማድረግ የሰራናቸውን ኃጢአቶች በመናዘዝ የክርስቶስን ስጋ እና ደም መቀበል ነው።ከሳምንት ውስጥ ስድስቱን ቀን እንዴት እንደምናሳልፍ ስንመለከት አምላካችንን ከማምለክ ይልቅ ለስልጣን ለገንዘብ ለዝና ለስኬትና ለደስታ ስንሰግድ ነው ራሳችንን የምናገኘው። ነገር ግን መስዋእተ ቅዳሴን ስናስቀድስ ልባችን ወደ አምላካችን ትመለሳለች፣ ቅዱስ ቁርባንን በምንቀበልበት ጊዜ ደግሞ እንቀደሳለን።

### ካቶሊካዊ ኃይማኖታችንን ይበልጥ ማወቅ

አንድ ተማሪ ኮሌጅ ሲገባ ዋና ተግባሩ ለመማር ለማጥናትና እውቀትን ለማስፋት እንደሆነ ሁሉ ከትምህርቱ ጎን ለጎን ኃይማኖታዊ እውቀቱን ለማሳደግ ማጥናቱ በእምነቱና በመንፈሳዊነቱ እንዲያድግ ያግዘዋል። እኛም በእምነታችን በየእለቱ እንድናድግ ካቶሊካዊ ኃማኖታችንን ይበልጥ እንወቅ። ቤተክርስቲያናችን የምታምነውና የምታስተምረውን ሁሉ ከምናውቀው የበለጠ ለማወቅ በግልም ሆነ በጋራ ማጥናትና መማማር ጠቃሚ ነው።

አምላካችን በእርሱና በሰዎች ፊት በመንፈሳዊነትና በእምነት ያሳድገን!

# “ገናን ለምንድን ነው የምናከብረው?”



በክቡር ካቲኪስት ወርቁ ጦጤ
ከኮንሶላታ ማርያም ቤተ ጸሎት

እግዚአብሔር ከኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በፊት በስምንተኛው መቶ ዓመት በነቢዩ ኢሳይያስ አማካይነት የተነገረው ትንቢት ማለትም “እነሆ ድንግል ትጸንሳለች፣ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፤ ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች” (ኢሳ. 7፥14)። የተባለው ትንቢት ጊዜውንና ሰአቱን ጠብቆ ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም ሥጋ ለብሶ ወደ እዚች ምድር ለእኛ ሰላም ሊሰጠን መጣ። እነሆ ኢየሱስ ክርስቶስ ከተወለደ እ.አ.አ. 2025 ዓ. ም. ሲሆን በእኛ በኢትዮጵያ አቆጣጠር ደግሞ 2017 ዓ. ም. ይሆናል።

ኢየሱስ ክርስቶስ“አማኑኤል” ሆኖ የአመጣጡን ሂደት ብናይ የሮማዊው ንጉሥ ቄሣር በግዛቱ በነበረው የሕዝብ ቁጥር እንዲደረግ በአዋጅ አዘዘ። ይህ ትዕዛዝ ሲሰማ ማለትም የኢየሱስ ክርስቶስ መወለድ ሰው ሁሉ ወደየትውልድ ሀገሩ ሊጻፍ ሄደ። ቅዱስ ዮሴፍ ከዳዊት ዘር ስለነበር ይቀመጥበት ከነበረው ናዝሬት ከተማ ነፍሰ ጡር ከነበረችው እጮኛው ከእመቤታችን ድንግል ማርያም ጋር ወደ ዳዊት ከተማ ወደ ቤተልሔም ሄዱ። በዚያም ሳሉ እመቤታችን ድንግል ማርያም የመውለጃዋ ቀን ደረሶ የበኩር ልጅዋን ኢየሱስ ክርስቶስን ወለደች።

የእንግዳ ማደሪያ ሥፍራ ስላለተገኘ በከብቶች በረት ወልዳ በጨርቅ ጠቅልላ በግርግም ውስጥ አስተኛችው።

በጨለማ ይኖር የነበረው ሕዝብ ታላቅ ብርሃን አየ። ሰው የአምላክን ትእዛዝ አፍርሶ ከተከለከለው ፍሬ ቀንጥሶ ከበላ በኋላ ኃጢአት በመሥራቱ ለመከራ ተጋለጠ፣ በአምላክ ጥላቻና እርግማን ወደቀ። ኑሮው ድህነት፣ ትግል፣ ስቃይ ብቻ ሆነ። ጨለማ ከበበው፣ የፀሐይን ብርሃን እንደማያይ ዓይነ ስውር ሆነ። እግዚአብሔር ምንም እንኳን ያን ጊዜ እጅግ አዝኖና ተቆጥቶ ሰውን ከፊቱ በመከራና በድኅነት እንዲሰቃይ ቢተውም መሐሪ ስለሆነ መከራውንና መጥፎ ሁኔታውን ተመልክቶ አሳዛኝ ኑሮውን አይቶ ራራለት።

አስቀድሞ በደግነቱ በእምነት እንደፈጠረው እንዲሁም ደግሞ ፊቱን መልሶ በምሕረቱ በጣም ከሚያሳዝን የኃጢአትና የባርነት ከባድ ኑሮው ነጻ ሊያወጣውና ከወደቀበት ጉድጓድ አውጥቶ ከፍ ሊያደርገው ወሰነ። እንደገና በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ አድርጎ የዘለዓለማዊ ደስታው ተከፋይ እንዲሆን ጠራው። ሰው ለዚህ ከአምላክ በተሰጠው ተስፋ ተጽናንቶ በጨለማ ኑሮ ሲጋደል ሳለ የድኅንነት ብርሃን ጮራ ፈነጠቀበት። “በጨለማና በሞት ጥላ ይኖር የነበረው ሕዝብ ትልቅ ብርሃን አየ” (ኢሳ. 9፥3)። የነቢዩ ኢሳይያስ ትንቢት ተፈጸመ።

እግዚአብሔር ከረጅም ዘመናት በፊት ለሰው አሰምቶት የነበረውን አዳኝ ከሰማይ ላከለት። ስለዚህ ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ቃል እንዲህ የሚለን “ጊዜው ሲደርስ እግዚአብሔር እነዚያን ከሕግ በታች የነበሩትን ለመዋጀት ከሴት የሚወለድ ሕግንም የሚከተል ልጁን ላከልን” (ገላ. 4፥4)።

መልአኩ ለእረኞች “ታላቅ የምሥራች ዛሬ መድኃኒት ተወልዶላችኋል፣ ለሕዝብ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች አመጣሁላችሁ በዳዊት ከተማ መድኃኒት ተወልዶላችኋል” (ኢሳ. 9፥7) አላቸው። የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ፍጹም ደስ የሚያሰኝ ታላቅ የምሥራች ነው። ምክንያቱም እርሱ ዓለምን ሁሉ ሊያድን ነው የመጣው። ስለዚህ ነው ነቢዩ ኢሳይያስ የእግዚአብሔርን ቃል እንዲህ ያለን “ሕፃን ተወልዶልናል ወንድ ልጅም ተሰጥቶናል” (ኢሳ. 9፥6)

ወደ ገፅ 5

**"መልካም ስጦታ ሁሉ ፥ ፍጹምም በረከት ሁሉ ፥ እንደ ጥላ መዘዋወር ወይም መለወጥ ከሌለበት ከላይ ከብርሃናት አባት ይወርዳሉ።" ያዕ. 1:17**

## ቤተሰብ



# ኢዮቤልዩ እና የቤተሰብ ጸሎት

በክቡር አቶ አርጋው ፋንቱ

(የቀጠለ)

እግዚአብሔር አምላክ የሰውን ልጅ ለማዳን የሰጠውን የተስፋ ቃል ዕውን ያደረገው በቤተሰብ በኩል በመምጣት ነው። ወልደ አምላክ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ፣ ከድንግል ተወልዶ፣ በቤተልሔም በከብቶች ግርግም ውስጥ ተጋርዶ፣ በከብቶች ተከልሎ፣ በመላእክት ዝማሬ ደምቆ፣ በሰብዓ ሰገል ስግደት ተከብሮ የተገለጠው ቤተሰብን ማዕከሉ አድርጎ ነው።

እነሆ ዛሬም ቤተክርስቲያን የጌታችን የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የልደት በዓል ስታከብር የሦስት ሺህኛውን የ25ኛ ዓመት ኢዮቤልዩ በዚሁ ወቅት በማብሰር ነው። ባለፈው ወር ጽሑፌ ላይ እንደተጠቀሰው ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፍራንቼስኮስ 2025 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ.) የኢዮቤልዩ ዓመት እንዲሆን ሲያውጁ ዲሴምበር 24 ቀን 2024 ዓ.ም.(እ.ኤ.አ.) (ታህሣሥ 15 ቀን 2017 ዓ.ም.) በሮም ቫቲካን የሚገኘውን የቅዱስ ጴጥሮስን ካቴድራል ቤተክርስቲያን ቅዱስ በር በመክፈት አስጀምረዋል።

ይህንን የኢዮቤልዩ ዓመት እንደቤተሰብ እንዴት መኖር እንዳለብን እንዲረዳን "እንድንጸልይ አስተምረን" በሚለው አጭር ትምህርታዊ እና ተግባራዊ የቤተሰብ ጸሎት አስተምህሮዋቸው ውስጥ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፍራንቼስኮስ በጣም ጠቃሚ ሀሳብ አንስተዋል። በመቀጠልም በነዚህ ሀሳቦች ላይ አተኩረን እንጋራ።

ስለ ቤተሰብ ጸሎት ሁለት መሠረታዊ ማሳያዎችን ይጠቅሳሉ። የመጀመሪያው ራሳቸው በመጋቢት ወር በ2016 (እ.ኤ.አ.) ካስተላለፉት "ፍቅር በቤተሰብ ውስጥ" በተሰኘው ሐዋርያዊ መልዕክታቸው ውስጥ በሚገኘው ላይ በማተኮር ነው። እንዲህም ይላሉ፡ "የቤተሰብ የጸሎት ልምምድ እና ለጸሎት የሚሰጥ ትኩረት ከማንኛውም የትምህርተ ክርስቶስ ትምሕረት ወይም ስብከት የበለጠ አቅም ያለው የስብከተ ወንጌል ማጠናከሪያ ነው።" (ቁ.288) ሲያጠቃልሉም፡ "በዚህ ዓይነት ልምምድ ላይ ተመሥርቶ ብቻ ነው ቤተክርስቲያን ለቤተሰብ ያላትን ሐዋርያዊ እንክብካቤ በማጠናከር ቤተሰቦች ትንሽዋ ቤተክርስቲያን እና በኅብረተሰብ ውስጥ የስብከተ ወንጌል እርሾ መሆን የሚችሉት።"(ቁ.290)።

በመቀጠልም ቅዱስ ዮሐንስ ጳውሎስ ዳግማዊ በ1984 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ.) 'ቤተሰብ በዘመናዊው ዓለም' በተሰኘው የቤተሰብ ሐዋርያዊ መልዕክታቸው ውስጥ ስለ የቤተሰብ የኅብረት ጸሎት አስፈላጊነት፡ "በቤተሰብ ውስጥ ሰብዓዊ ሰው ሰው ወደመሆን ብቻ እና በትምሕረት መሣሪያነት በተከታታይ እየተገነዘበ ወደ ሰብዓዊ ማኅበረሰብ መቀላቀል ብቻ ሳይሆን፡ ነገር ግን በምስጢረ ጥምቀት በዳግም መወለድ እና ስለ እምነቱ በመማር ልጅ የእግዚአብሔር ቤተሰብ ወደ ሆነችው ቤተክርስቲያን ይቀላቀላል።" (ቁ.15) ያሉትን በአጽንዖት ጠቅሰዋል።

ቤተሰብ በጸሎት መትጋት እና መሳተፍ ያለባቸውን ሦስት ሁነቶች እንደማሳያ አንስተዋል። እነርሱም በማዕድ ጊዜ በሚደገም ጸሎት፣ በቀን መጀመሪያ እና ማብቂያ ላይ በሚደገም ጸሎት እና በሰንበት ዕለት በሚደገም ጸሎት ላይ አተኩረዋል።

## በማዕድ ጊዜ በሚደገም ጸሎት

ቤተሰብ በዋናነት ከሚሰባሰብባቸው ጊዜያት አንዱ በማዕድ ጊዜ ነው። ማንኛውም ቤተሰብ ቢያንስ በቀን አንድ ጊዜ ለማዕድ መሰባሰቡ አይቀርም። ይህ ጊዜ አጭር ቢሆንም ቤተሰብ አብሮ ለመጸለይ ትልቅ ትርጉም ያለው ጊዜ ነው። ለተገኘው ማዕድ ጌታን ማመስገን እና ምግብ ለሚያስፈልጋቸው መጸለይ ተገቢ ነው። በአባታችን ሆይ ጸሎት ጊዜ የምንደግመውን 'የዕለት እንጀራችንን ስጠን' ጸሎት ትክክለኛ ትርጉም ልጆች የሚገነዘቡት በዚህን ጊዜ ነው። የምንቋደሰው ማዕድም በሕይወት እስካለን ድረስ ከሰማያዊ አባታችን የምናገኘው የመለኮታዊ ቡራኬ መሆኑን እየተገነዘቡ ያድጋሉ። ስለዚህ ቤተሰብ ማዕድ ሲጀመር እና ሲያበቃ አብሮ መጸለይን መለማመዱ በብዙ መንገድ ጠቃሚ ነው። በማዕድ ጊዜ አብሮ የሚደገም ጸሎት ቤተሰብን፣ የማዕድ በረከትን እና በረከቱን ሰጪውን አምላክ ያገናኛል።

## በቀን መጀመሪያ እና ማብቂያ ላይ በሚደገም ጸሎት

ሌላው ለቤተሰብ ጸሎት ምቹ ሁኔታ ልጆች ወደ መኝታቸው ሲሄዱ ነው። በሰላም ስላለፈው ቀን፣ ስለታመሙ ዘመዶች፣ በጨዋታ ስላለፈው ጊዜ ማመስገን እና በመሳሰሉት ጉዳዮች ላይ መጸለይ ልጆች በዕለቱ ከጌታ ስላገኙት በረከቶች እንዲያስቡ ያግዛቸዋል። በዚህ ጸሎት ማብቂያ ላይ የተኮራረፉ ካሉም እርስበርስ ይቅር እንዲባባሉም ዕድል ይፈጥራል። ር.ሊ.ቃነ ጳጳሳት ፍራንቼስኮስ፡ "ሰላም ሳትፈጥሩ ቀኑን አትጨርሱት!" ይላሉ። በቤተክርስቲያን ሥርዓት የተለመዱት የጠዋት እና የማታ ጸሎቶች የዚህ ልምድ ውጤቶች ናቸውና የየቤተሰቡ ክርስቲያናዊ ልምድ ሊሆኑ ይገባል።

## በሰንበት ዕለት በሚደገም ጸሎት

በብዙ ቤተሰብ ያልተለመደ፡ ነገር ግን ሊለመድ እና ሊተገበር የሚገባው የቤተሰብ የመዝሙረ ዳዊት አብሮ የመጸለይ ልምድ ነው። በተለይም ቅዳሜ ማታ ለእሑድ ጠዋት መስዋዕተ ቅዳሴ ተሳትፎ ዝግጅት ይሆን ዘንድ የሚደገም የቤተሰብ መዝሙረ ዳዊት ነው። መዝሙረ ዳዊት በመድገም ውስጥ የእሑድ ንባባትን በቤተሰብ አባላት በየተራ እየተነበበ ለእሑድ የመስዋዕተ ቅዳሴ ተሳትፎ እና ስብከተ ወንጌልን በብቁ ዝግጅት ለማዳመጥ ዕድል ይሰጣል። ይህ ብቻ አይደለም። ልጆች እንደየዕድሜ ዕድገታቸው በየተራ ከመጽሐፍ ቅዱስ ንባባት ማንበብ ሲለማመዱ የማንበብ እና ያነበቡትን የመረዳት አቅማቸውን ይጨምርላቸዋል። ከንባቡ በኋላ ከቤተሰብ አባላት አንዱ (አባት ወይም እናት) በተረዱት መጠን የንባቡን አጭር አስተንትኖ ለልጆቻቸው ቢያጋሩ አብሮ የማደጉ ዝንባሌ ይጠናከራል። በሌሎችም ዘንድ የመልካም ቤተሰብ አብነት የመሆንን ትሩፋት ያሰፋል።

እንደሁኔታው የቤተሰብ የመዝሙረ ዳዊት ጸሎት በየማታውም አብሮ ሊደገም ይችላል። የመዝሙረ ዳዊት ብቻ ሳይሆን አልፎ አልፎም የቤተሰብ የመቁጠሪያ ጸሎት አብሮ መድገም ቤተሰባዊ አብሮነትን ያጠነክረዋል፤ ዓለማዊ እና ሰይጣናዊ ፈተናን ያርቃል፤ መተባበርን፣ መከባበርን፣ መተሳሰብን በእጅጉ ያሳድገዋል።

ር.ሊ.ቃነ ጳጳሳት በቤተሰብ ጸሎት ሀሳብ ላይ በመጨረሻ የሚጨምሩት በተለይ ለአዳጊዎች እንደሁኔታው እና እንደጊዜው የዕለቱን ቅዱስ በማሰብ የቅዱሱን የሕይወት ታሪክ ለልጆች ማጋራት በጣም ጠቃሚ ነው፡ ይላሉ። ለምን እና እንዴት ቅዱስ እንደሆነ/ሆነች ማብራራት እና አማላጅነቱን/ቷን መጠየቅን መለማመድ ተገቢ ነው።

ወድ ወገኖች የጌታችን የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የልደት በዓል ስናስብ እና ስናከብር፣ ቤተክርስቲያን ያሳሰበችንን የኢዮቤልዩዓመትስናከብርእንደክርስቲያንቤተሰብበቤተሰባችን ውስጥ የለመድነው የጸሎት ሕይወት ምን ይመስላል? የትኛው የጸሎት ልምድ ኖሮን የትኛው ጎደለን? ለልጆቻችን ዕድገት እና አስፈላጊ ነገሮችን ለማሟላት ከምናደርገው ዕለታዊ ሩጫ ባሻገር አብሮ ለመጸለይ የምንሰጠው ጊዜ ምን ያህሉን ነው? የሚሉትንና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች ለየራሳችን እናንሳ።

በቤተሰብ ውስጥ ተወልዶ "በጥበብና በቁመት በሞገስም በእግዚብሔርና በሰው ፊት"(ሉቃ.2፡52) ያደገው የቤተልሔሙ በረከት ክርስቶስ ኢየሱስ ልደቱን በማክበር፣ የኢዮቤልዩን ዓመት በትጋት በመኖር እና በቤተሰብ ጸሎት ጠንካራ ተሳታፊዎች ሆነን እንኖር ዘንድ ፀጋና በረከቱን ያብዛልን። የተባረከ የልደት በዓል! ለሁላችንም። አሜን።

### "ገናን ለምንድን ...

ከገፅ 4 የዞረ

ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስም የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ይለናል፡- "ቃልም ሥጋ ሆነ ጸጋንና እውነትንም ተሞልቶ በእኛ አደረ አንደ ልጁም በአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነውን ክብሩን አየን" (ዮሐ. 1፡14)።

ከላይ በተገለጠው ሁኔታ ኢየሱስ ክርስቶስ የአዳም ልጆችን ከኃጢአት ኑሮና ከሰይጣን ባርነት ሊያወጣቸውና ከውድቀት ሊያነሳቸው እና ከአምላካቸው ጋር ሊያስታርቃቸው በድንግል ማሕጸን በማደር የሰው ሥጋ ለብሶ ወደ ምድር ወረደ። እስከ ዕለተ ሞቱ በመስቀል ላይ የሕይወቱን ዘመን እንደማንኛውም ተራ ሠራተኛ ለመኖር ሥራ እየሠራ አሳለፈ። ለወንድሞቹ ለአዳም ልጆች የጨለማን የውድቀት ጊዜ አስወግዶ የብርሃን ተስፋ ከፈተላቸው። የስቃይና የኃዘን ዘመን ደምስሶ የደስታና የምቾት ዘመን እንዲያመጣላቸው ከድንግል ማርያም ተወለደ።

በዚህ የምሕረት ተግባር የመድኃኒታችንና የአምላካችን ደግነት ተገለጠ። ስለዚህ ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ቃል እንዲህ የሚለን፡- "የእግዚአብሔር ምሕረት ብዙ ከመሆኑና ለእኛም ያለው ፍቅር ታላቅ በመሆኑ የተነሣ ምንም እንኳን በበደላችን የሞትን ብንሆንም እግዚአብሔር ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ሕይወትን ሰጥቶናል እናንተም የዳናችሁት በጸጋው ነው" (ኤፌ. 2፡4)።

በትዕቢት የተኰነነው ሰው በአምላክ ልጅ ትሕትና ከወደቀበት ገደልና አዘቅት ወጣ። ምስኪን በዲያብሎስ ተታሎ በሞኝነት እከብራለሁ ብሎ ለውርደት የተዳረገው ሰው በአምላክ ልጅ ውርደት በበደሉ ያጠፋውን ክብር እንደገና አገኘ።

ከመጀመሪያ ይበልጥ ከፍ አለ፤ በልዑል ወንበር ከመላእክት ጐን ሊቀመጥ ቻለ። ቅዱስ ልዮን እንዲህ ይላል "ወልድ የእግዚአብሔር ልጆች እንዲያደርገን ሰው ሆነ" በኢየሱስ ክርስቶስልደት አምላክና ሰው ታርቀው ሰላም ያደረጉበት የተባረከና የተቀደሰ ቀን ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ተወልዶ ወደ ዓለም ሲመጣ በሰማይም በምድርም ታላቅ ደስታ ሆነ። "እግዚአብሔር በሰማይ ክብር ይሁን በምድርም እግዚአብሔር ለሚወዳቸው ሰዎች ሰላም ይሁን እያሉ መላእክት ዘመሩ" (ሉቃ. 2፡14)።

በኢየሱስ ክርስቶስ ልደት እግዚአብሔር ከበረ ተመሰገነ። የፈለገው ካሣ እንደ መስዋዕት ቀለበሰለት። ሰው ደግሞ ከሰይጣን ባርነት ነጻ ወጥቶ ሰላምን አገኘ። ዛሬ በቤተክርስቲያን በኢየሱስ ክርስቶስክርስቶስ ልደት ምክንያት ተደስተን እንገኛለን። የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የልደቱን በዓል ስናከብር፡-

1. ሰላማችንና ደኅንነታችን የሆነውን ሕፃን ማመስገን አለብን።
2. ልደቱን ለእኛ የነፍሳችን ልደት እና የነፍሳችን መታደስ ሊሆነን ያስፈልጋል።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ቃል "የጨለማን ሥራ ትተን የብርሃን ጦር እንልበስ" እንዳለን እኛም ኢየሱስ ክርስቶስ ያመጣልንን ሰማያዊ መንፈስ መልበስ ያስፈልገናል። ሕፃኑ ኢየሱስ ክርስቶስ ለመምሰል መንገዱን መያዝ ያስፈልገናል። አሁን አዳኛችን ተወልዶልናልና ሰላምን እንከተላት። ከዚህ በመለኮታዊ ሕፃን አማካይነት ሰላምና የአምላክ ደህንነት መጣልን። የተገኘውን ሰማያዊ ሀብት በጥንቃቄ መጠበቅ ያስፈልገናል። ምክንያቱም ዋጋው አለመጠን ውድ ነውና። ለሕይወታችን ዋስትና የሚሆነንን ሰማያዊ ሰላም እንዳናጠፋ ከዚህ ከተባረከ መለኮታዊ ሕፃን እንዳንርቅ ጠበቅ አድርገን መከተል ያስፈልገናል።

የተወለደው ሕፃኑ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰላሙን ለእኛ ዘወትር አብዝቶ ይስጠን።

ዛሬ በዓለማችንና በሀገራችን ትልቅ በረከት የጠፋው የኢየሱስ ክርስቶስ ሰላም ስለጠፋ ስለሆነ የሰላሙ ንጉሥ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰላሙን ለሀገራችንንና ለዓለማችን ይስጠን። መንፈስ ቅዱስም ለሀገራችን ይሁን ለዓለም መሪዎች ሕዝባቸውን በቅንነትና በትህትና ማስተዳደር ይችሉ ዘንድ መንፈሳዊ ጥበብንና ዕውቀትን ዘወትር አብዝቶ ይስጣቸው።

መልካም የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ይሁንልን።

**"በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።" ዮሐ. 3:16**

# የቃሉ ውበት

# "ነገር ግን እንደ ሰው ሆኖ በመወለድ የባርያን መልክ ይዞ ራሱን ባዶ አደረገ "ፊል 2፡ 7

በክቡር አባ ዳንኤል አሰፋ

**ሥርጉት፡-** የገና በዓል ምሥጢር በጣም ይደንቀኛል። ባለፈው ስለ ፍቅር ብዙ ተወያይተን ነበር። እኔ ግን አሁንም ብንቀጥል እላለሁ።

**ሳሙኤል፡-** ወደ ሌላ ርእስ ብንሄድስ?

**ሥርጉት፡-** ኧረ የፍቅር ነገር እኮ በጣም ሰፊ ነው።

**ሳሙኤል፡-** ወደዛ መመለሳችን አይቀርም። ዛሬ ግን ስለ ገና ምሥጢር ብንመራመር በጣም ደስ ይለኛል።

**ሥርጉት፡-** ስለ ገናም እኮ ከዚህ በፊት ተወያይተን ነበር።

**ኀሊና፡-** የገናም ምሥጥር እኮ ብንመራመር፣ ብንመራመር የማንጨርሰው ነው። ልክ እንደ ፍቅር ምሥጢር።

**ሥርጉት፡-** ገና የፍቅር መወለድ ምሥጢር አይደለም እንዴ?

**ሳሙኤል፡-** እኔ የሚገርመኝ የጊዜ ጉዳይ ነው።

**ሥርጉት፡-** ስለ ጊዜ ምን ማለት ፈልገህ ነው።

**ሳሙኤል፡-** እግዚአብሔር ዘላለማዊ ነው አይደል?

**ኀሊና፡-** አዎን ነው።

**ሳሙኤል፡-** ታድያ ዘላለማዊ ሆኖ እንዴት በሰው ጊዜና ዘመን ውስጥ ይገባል?

**ጥበቡ፡-** የዚህ ልጅ ማደጉ ብቻ ሳይሆን የሚደንቀኝ የሚያነሣቸው ጥያቄዎችም ጭምር እየደነቁኝ ነው።

**ኀሊና፡-** ጠያቂ አዋቂ ይባል የለም። መጠየቁ ጥሩ ምልክት ነው እላለሁ በበኩሌ።

**ሥርጉት፡-** እስቲ በጊዜና በዘላለማዊነት መካከል ያለውን ልዩነት ግለጽ።

**ጥበቡ፡-** አሁን ከባድ ጥያቄ አመጣሽ።

**ሳሙኤል፡-** ዘላለማዊነት ከጊዜ በጣም የተለየ ይመስለኛል። ለዚህም ነው የገና ምሥጢር ይደንቀኛል የምለው።

**ጥበቡ፡-** ዘላለማዊ ማለት መጨረሻ የሌለው ጊዜ ብለን መረዳት አንችልም?

**ሳሙኤል፡-** ለእኔ ዘላለማዊነት መጨረሻ የሌለው በሚለው መረዳት የሚቻል አይመስለኝም።

**ጥበቡ፡-** ለምን?

**ሳሙኤል፡-** መጨረሻ የሌለው ጊዜ ስንል እኮ አሁንም ስለ ጊዜ እየተናገርን ነው።

**ጥበቡ፡-** ታዲያ ከዚህ ውጭ እንዴት መናገር እንችላለን?

**ሳሙኤል፡-** ጊዜ የተፈጠረ ነገር ነው፤ ዘላለማዊ ሕይወት ግን ከጊዜና ከቦታ ባሻገር ሕይወት ስለሆነ በጊዜ መተርጐም አሳንሶ ማየት ይመስለኛል።

**ኀሊና፡-** እዚህ ላይ፣ የቅዱስ አውጎስጢኖስ ኑዛዜ ትዝ አለኝ።

**ጥበቡ፡-** እንዴት?

**ኀሊና፡-** የጊዜንና የዘላለማዊነትን ምሥጢር ስለ መረመረ ነዋ!

**ጥበቡ፡-** ኑዛዜ የንስሐና የእምነት ምስክርነት መጽሐፍ አይደል እንዴ?

**ኀሊና፡-** እሱ የሚገርም ነገር ነው። በጸሎት ውስጥ ጥልቅ የሆኑ፣ የሚያመራምሩ፣ ፈላስፋዎችን የሚያስደምሙ ነገሮችም አሉ። ከእነዚህም አንድ የጊዜ ምሥጢር ነው።

**ጥበቡ፡-** ጸሎት ለምስጋና፣ ለንስሐና ለልመና አይደለም የሚያስፈልገው። ለምርምርም ይሆናል ማለት ነው?

**ኀሊና፡-** ቅዱስ አውጎስጢኖስ እኮ ያመሰግናል፤ ንስሐም ይገባል፤ ልመናም ያቀርባል። ሆኖም በእነዚህ ሦስት ነገሮች ብቻ አይወሰንም። እግዚአብሔርን ይጠይቃል። ስለሚገርሙት ነገሮች ከፈጣሪ ጋር ይወያያል። በዚሁ አጋጣሚ ነው "ጌታ ሆይ፣ ጊዜ ምንድነው?" ብሎ የጸለየው። ሲጨምርም "ሰው ካልጠየቀኝ አውቃለሁ፤ ሰው ግን ከጠየቀኝ አላውቀውም፤ " ይላል። ቀጠል አድርጎም፣ እንደ ጊዜ የሚቀርበን፣ እንደ ጊዜም ምሥጢራዊ ነገር እንደሌለ ያስረዳል።

**ሳሙኤል፡-** በደንብ እስማማለሁ። መገረም እና መደነቅ በመንፈሳዊ ሕይወት ውስጥም ትልቅ ቦታ አለው ማለት ነው።

**ሥርጉት፡-** እንደሚመስለኝ ከሳሙኤል ፍልስፍና ብንወጣና ስለ ገና ምሥጢር ብንወያይ ይሻላል።

**ሳሙኤል፡-** እንዴ፣ እኔ እኮ ያነሣሁት ነጥብ የገናን ምሥጢር ለማድነቅ ነው።

**ሥርጉት፡-** እንዴት ነው የምታደንቀው?

**ሳሙኤል፡-** በገና የምናከብረው ልደት ከልደቶች ሁሉ የተለየ ልደት ነው፤ የማይወለደው ተወለደ። ከጊዜ ውጭ ያለው በጊዜ ውስጥ፣ በጊዜያችን ውስጥ ገባ። ከቦታ ውጭ የሆነው ጌታ በበረት ውስጥ ተኛ። ከዚህ የሚበልጥ የሚያስደንቅ ምን አለ? ከዚህ የሚበልጥ ምን ዓይነት ትሕትና አለ? ከዚህ የሚበልጥ ምን ዓይነት ተአምር አለ?

**ኀሊና፡-** ያነሣሃቸው ነጥቦች በጣም አስደስተውኛል። በከፈትከው መንገድ ብንሄድ፣ ወደ ፊሊጵስዩስ መልእክት እና ወደ ገና ምሥጢር መድረስ እንችላለን። ፍቅርና ትሕትና የእግዚአብሔር ልጅ ከሰማየ ሰማያት አወረደው። የባርያን መልክ ወስዶ፣ ከኃጢአት በስተቀር በሁሉም የሰውን ሕይወት ኖረ። በከፊል ይታይ የነበረውን የእግዚአብሔር ክብር በሙላት ገለጸው።

**ጥበቡ፡-** በከፊል ተገልጦ የነበረው ክብር ስትይ አልገባኝም።

**ኀሊና፡-** የእግዚአብሔር ክብር ለሙሴ ተገልጦለት ነበር። እንዲያውም ከማንም ነቢይ በላይ እግዚአብሔር ከሙሴ ጋር ይነጋገር እንደነበር ብሉይ ኪዳን ያስተምራል። ሰው ከወዳጁ ጋር እንደሚነጋገር እግዚአብሔር ከሙሴ ጋር ይነጋገር ነበር ተብሎ ተጽፏል። ሙሴ በተራራ ላይ የተመሰጠው የእግዚአብሔር ክብር ስለማረከው ነበር። ነገር ግን ዘጸ 33 ላይ ሙሴ እግዚአብሔርን እያየ፣ የሚቀረው እንዳለ ለማሳየት "ክብርህን አሳየኝ" ብሎ ይጠይቃል።

**ሳሙኤል፡-** በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ፣ የእግዚአብሔር ክብር በክርስቶስ እንዴት እንደሚገለጥ በተደጋጋሚ ይገኛል። የዮሐንስ ወንጌል በአብ እቅፍ ያለው ወልድ ሥጋ በመልበሱ የእግዚአብሔርን ክብር እንዴት በሙላት እንደገለጸው ያስረዳል። በዚሁ ወንጌል ክርስቶስን ያዩ ሐዋርያት፣ አብን እንዳዩ ተነግሯቸዋል። ወደ ወንጌሉ መጨረሻ፣ ዮሐ 18፣ ክርስቶስን ለመያዝ የመጡ ወታደሮች "እኔ ነኝ" የሚለውን የክርስቶስ ድምጽ ሰምተው፣ ወደ ኋላ አፈግፍገው ወድቀዋል። ክርስቶስም ወደ ሕማማቱ ሲሄድ በታላቅ ግርማና ክብር ነበር።

**ሥርጉት፡-** ይህ እንዴት ነው ከገና ምሥጢር ጋር የሚገናኘው?

**ኀሊና፡-** አሁን ሳሙኤል የጠቀሳቸው ነጥቦች በሙሉ የገና፣ የልደት ምሥጢር ውጤቶች ናቸው ማለት የሚቻል ይመስለኛል። በእኛ ጊዜ ውስጥ የገባው ጌታ ያለፈውን ይፈውሳል። የሚመጣውንም ይቀድሳል። በጊዜ ውጥረት የሚከሠተውን ጭንቀት ይበትናል። ከጊዜ ቀንበር ነጻ ያወጣናል።

**ጥበቡ፡-** የልደት ባለቤት የሆነው ጌታ ጊዜያችንን ይባርክልን። እሱ ወደ እኛ የሚመጣበት ጊዜ ትዝታችንና የወደፊታችን የሚቀደስበት ወቅት ይሁንልን።

**ሁሉም**፤ አሜን

## የጸሎት ሐዋርያነት

**<u>ጥር</u>**

*<u>ትምሕረት የማገኘት መብት</u>*

በጦርነት ምክንያት በስደት ያሉ እንዲሁም የትምሕረት እድል የተነፈጋቸው ሁሉ ነገ የተሻለ ዓለም ለመገንባት የሚያስችላቸውን ትምሕረት የማገኘት መብታቸው እንዲከበርላቸው እንፀልይ።

**<u>January</u>**

***<u>For the right to an education</u>***

**Let us pray for migrants, refugees and those affected by war, that their right to an education, which is necessary to build a better world, might always be respected.**



**<u>የማቅረቢያ ጸሎት</u>**

*ቅዱስ አባት ሆይ*
*ሁሌም ከእኔ ጋር እንደምትሆን አምናለሁ ፤ ልቤን በየቀኑ በቅዱስ ቁርባን ራሱን በሚሰጠን በልጅህ በኢየሱስ ልብ ውስጥ አኖራለሁ። ቅዱስ መንፈስህ እኔን ወዳጅህ እና ሐዋርያህ ያድርገኝ ለአገልግሎትም ዝግጁ እና ቀናኢ ያድርገኝ። ደስታዬን፣ ስቃዬን፣ ተስፋዬን፣ ሥራዬን፣ ሁሉ ነገሬን በዓለም ካሉት የፀሎት ሐዋርያቶች ጋር በአንተ እጅ አኖራለሁ። ከእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ጋር ቀኔን ለቤተክርስቲያን ተልዕኮ አቀርባለሁ! በር.ሊ.ጳ የፀሎት ሐሳብም እፀልያለሁ!*

## የአዲስ አበባ...

ከገፅ 1 የዞረ

በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ሰበካዊ የምክክር ጉባኤ በዳግማዊ ዮሐንስ ጳውሎስ የወጣቶች ማዕከል ማካሄድ አካሄደ። ጉባኤውን በፀሎት ያስጀመሩት ብፁዕ ካርዲናል አቡነ ብርሃነኢየሱስ ሱራፌል ሊቀጳጳሳት ዘካቶሊካውያን፣ ከአስር ዓመት በፊት የተካሄደውን ሰበካዊ ጉባኤ በማውሳት፣ አሁን ላይ በርካታ ለውጦች መኖራቸውን በመጥቀስ ከዓመታት በኋላ የሚደረገውን ሰበካዊ ጉባኤ ተሳታፊዎች በአትኩሮት እንዲከታተሉ አፅንኦት ሰጥተዋል።

የጉባኤውን የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ሐዋሪያዊ ማስተባበሪያ ፅህፈት ቤት ሀላፊ ክቡር አባ ጴጥሮስ በርጋ ይህ ጉባኤ እየተካሄደ ያለው ሰበካዊ ጉባኤው ከ10 ዓመት በፊት ባደረገው ጉባኤ ያስተላለፋቸውን ውሳኔዎችና ያከናወናቸውን ተግባራት ለመገምገም መሆኑን ጠቅሰዉ፣ የያዝነው አመት የተስፋ ነጋዲያን እንደመሆኑ ቤተክርስቲያን የሰጠችንን ሃብት ጥቅም ላይ ማዋል ላይ የተመረኮዘ ስራ መሰራት እንዳለበት ተናግረዋል። "በእግዚአብሔር ላይ ያለን ተስፋ እግዚአብሔር ወደፊት ስለሚሰጠን ሥጦታ የተቀበልነውን ቃልኪዳን ተስፋ እንድናደርግ ያስችለናል" ብለዋል።

የሰበካውን ያለፉት 10 ዓመታት ጉዞ በተመለከተ ከሐዋሪያዊ ማስተባበሪያ ፅህፈት ቤቱ ለጉባኤው ፅሑፍ ያቀረቡት አቶ ሰለሞን ደጀኔ ሥርዓተ አምልኮ፣ ቅዱሳት ሚሥጢራት፣ትምህርተ ክርስቶስ፣የካህናትና ምዕመናን ህንፀት ላይ፣ ፍትሕና ሠላም ላይ ሥራዎች እየተሰሩ መሆኑን በማንሳት በቂ እንዳልሆነና በቀጣይ አጠናክሮ መስራት አስፈላጊ መሆኑን ለጉባኤው አንስተዋል።

የማህበራዊ ዘርፍ አገልግሎት ሀላፊ አቶ አማን ደግፍ በጤና፣ በትምሕረትና በመልሶ ማቋቋም ዘርፎች ባለፉት አስር ዓመታት የተሰሩ ስራዎችንና ያገጠሙ ተግዳሮቶችን በዝርዝር ለጉባኤው አቅርበዋል። የበጀት ውስንነት፣ተቀናጅቶ የመሥራት ችግር፣መልሶ ማቋቋም ሥራ ላይ የመስሪያ ቦታዎች አለመኖር ችግሮች መኖራቸውን ጠቅሰዋል። በቀጣይ ጊዜያት በምግብ ዋስትና፣ በእርሻ ሥራ፣በውሃ ፕሮጀክቶች፣በአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ፣ በአካባቢ ጥበቃ ላይ የህብረተሰቡን ኑሮ ለማሻሻል ከመንግስት ጋር በጋራ ለመሥራት እቅድ እንደተያዘ ገልፀዋል።

*ምንጭ ሰላም ካቶሊክ ቴሌቭዥን*

**"ልጅም ትወልዳለች፤ እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ።" ማቴ.1:21**

LINK

No. 272 December 2024 P. O. Box 2454 Tel. (0111) 55 03 00 Addis Ababa

You are most welcome to
Subscribe and Advertise on LINK

# Message of His Eminence Cardinal Berhaneyesus President of Catholic Bishops' Conference of Ethiopia to all Faithful for the Solemnity of the Nativity of the Lord - January 2024

In The Name of The Father and of The Son and of The Holy Spirit. Amen!

## "But when the fullness of the time came, God sent forth his Son, born of a woman, born under the law"

**(Galatians 4:4)**

*Excellency Bishops,*
*Reverend Fathers, Religious Men and Women,*
*All People of Good Will,*
*All People of God,*
*All Ethiopians and Ethiopian Diaspora Communities*

To all the faithful and the family of God preparing to celebrate the Nativity of our Lord, I extend my heartfelt wishes for a peaceful and joyful celebration of the birth of our Lord and Savior, Jesus Christ. As we mark this sacred occasion, I send you this pastoral message to express my deep gratitude to God for His grace and mercy, which have allowed us to gather in safety and unity to celebrate this momentous day.

Each year, we come together to celebrate the Nativity of the Lord, a birth unlike any other. While it is customary to commemorate the birthdays of individuals who have made significant contributions to specific fields or to humanity, the birth of Christ invites us to reflect on something far greater. This celebration calls us to ask: What did Christ accomplish? What did He teach? What did He bring to the world? Such questions deepen our understanding of the profound significance of Christ's Nativity.

As we celebrate His birth, our thoughts should encompass not only His arrival but also His baptism, His teachings, His miracles, His suffering, His death, and His glorious resurrection. These reflections reveal the fullness of His life and the boundless love He brought to humanity.

Our celebration today should extend beyond the life within the church, reaching into our families and communities. In the Gospels, we see the Pharisees frequently opposing the teachings of Christ. What lessons can we draw from their actions? This is an opportunity for us to examine our own lives and identify moments where we might reflect similar attitudes.

As we celebrate the Nativity of the Lord, we are reminded of Christ's words: "Unless you become like little children, you will never enter the kingdom of God" (Matthew 18:3). Just as children depend on their parents or guardians, the Nativity of Christ invites us to recognize and embrace our dependence on God.

When we fully grasp this truth, the significance of Christ's birth shines brightly in our hearts, filling us with joy and bringing profound meaning to our lives.

Two thousand years ago, the apostles left behind their daily lives to follow Christ, captivated by His presence and teachings. Christmas, therefore, is a glorious occasion for us to reflect on how much space Christ holds in our own daily lives. It is a time to bridge the gap between our celebrations and our daily living, carrying the spirit of the holiday into our hearts and actions throughout the year. When our Lord Jesus Christ died on the cross, a Roman centurion declared, "Truly, He was the Son of God" (Matthew 27:54). This powerful testimony reminds us that the Nativity is not just the celebration of a remarkable figure's birth but the birth of the very Son of God. This understanding elevates the Nativity far above the commemoration of worldly greatness. In essence, Christmas is truly celebrated in our hearts and within our society when we seek to know and live out the works and teachings of Christ.

The Nativity of our Lord Jesus Christ entered human history, transcending the boundaries of time. The Creator of time and the Lord of all entered our world to dwell among us. As humans, we often dwell on the past, filled with memories that may bring regret or sorrow. We also look to the future with hope, but at times with fear and uncertainty. In these moments, it is our Lord and Savior Jesus Christ, whose birth we celebrate today, who brings us comfort. He is the One who redeems us from the sorrows of the past, healing our wounds, and who delivers us from the fears of the future, giving us hope and assurance. As Saint Paul reminds us in his letter to the Romans, "In this hope we were saved" (Romans 8:24). It is the child Jesus, born in a humble manger, who saves and comforts us. He is the Son of God, who came to visit and redeem humanity, the very creation made in His image and likeness.

In our time, humanity often acts as though it can achieve anything without God. Yet, this self-reliance leads to darkness and destructive thoughts, leaving many immersed in confusion and despair. Devoid of God's presence, people lose the true meaning of life and attempt to fill the void with fleeting, worldly things that offer no lasting peace. In this state, morality is devalued, the grace of sharing is denied, and the pursuit of power, honor, and comfort takes precedence over human dignity. Despite acquiring much, humanity struggles to live with moderation, forgetting to say, "enough." Compassion for the hungry and oppressed, who are created in God's image and likeness, fades away. Without faith, hope, and love, neither individuals nor societies can endure. A life or society that refuses to make room for God cannot make room for hope. Human philosophies, while valuable, have their limits. When touched and blessed by God, however, they can achieve far greater things and lead us toward true fulfillment.

Humanity was created for true happiness and eternal life, and Christmas brings us the joyful news of this truth. The Lord, the source of all joy, was born to fill our lives with gladness and to free us from the pain of loneliness. The light that dispels our darkness has come, and the wisdom that overcomes our ignorance has been born. The Lord who saves us from selfishness came to offer us life, and Emmanuel, "God with us," was born to free us from fear. Let us open the doors and windows of our hearts to let this good news bring comfort to our families and homes. Let us cherish this message, storing it as a treasure in the depths of our hearts. When we do so, the birth of the Lord will become the guiding light that directs the course of our lives.

Dear Faithful, let us pray that this celebration of the Lord's birth strengthens our faith, inspires us to strive for justice, and fills our hearts with compassion for those in need. May this Nativity celebration draw us closer to God and remind us that true joy is found in Him alone. Let the words of the prophet Isaiah echo in our hearts:

"For unto us a child is born, unto us a son is given, and the government shall be upon his shoulder: and his name shall be called Wonderful, Counselor, The Mighty God, The Everlasting Father, The Prince of Peace. If the increase of his government and peace there shall be no end. To establish his kingdom with judgment and righteousness from henceforth even forever. And he shall sit upon the throne of David, ruling over his land: for the zeal of the Lord God, the Everlasting Father, will accomplish this" (Isaiah 9:5-6).

This prophetic message should resonate deeply with us as we reflect on the Nativity. It challenges us to ask: Amid humanity's advancements in knowledge, technology, and other fields, how much have we progressed in morality, kindness, and goodness? We must ask ourselves further: How far have we moved away from war, hatred, envy, injustice, and deceit? If these remain unresolved, can we truly say humanity has grown? Humanity cannot fully understand itself merely by studying the world around it. True self-discovery comes from examining our hearts and recognizing that Christ, the source of life, is the One who lifts us from misery and rescues us from the abyss into which we have fallen. As we celebrate His birth, let us remember that the newborn child invites us to grow alongside Him. This celebration reminds us that the Lord has come, enabling us to achieve what we cannot accomplish on our own.

When our Savior, Jesus Christ, was born, the angelic proclamation of "peace on earth" resonated across the world, underscoring the profound importance of peace. However, true peace is not achieved merely through external actions or aspirations—it is cultivated through acts of justice and righteousness that reflect genuine love for one another. There is no greater path to peace than living by the principle of seeing others as ourselves and refraining from doing to others what we would not want done to us. This foundational truth guides us toward harmony and mutual respect in our relationships and communities. Therefore, it is the enduring hope and prayer of our Church that this justice and righteousness, which are essential for a peaceful and meaningful life, take root and flourish in our countries, guiding us all toward unity and peace.

Since all are equal before God, He created humanity to live on this fertile earth in peace and happiness. It is the will of God that His creation thrives in harmony, free from division and strife. Our Church continuously prays for the removal of evil and hatred from our land and for our country to be abundantly blessed. May the God of peace grant us His divine peace, love, and unity. We fervently pray that suffering and hardship, sorrow and misery, war and persecution be banished from our nation. May peace and love reign among our people, bringing healing, hope, and prosperity to all.

Finally, may this holiday be a time of peace and joy, filled with compassion and understanding. May the sick find healing, and may God grant peace and tranquility to those in distress and suffering. May He comfort those exiled from their homeland and homes, remember those in prisons, and bring solace to the sorrowful. May He encourage children who have lost their parents and welcome the departed into His eternal kingdom.

May the baby Jesus, the King of Peace, bless our country and the entire world with His peace.

Wishing you all a blessed Feast of the Solemnity of the Nativity of Jesus Christ.

*† Cardinal Berhaneyesus D. Souraphiel CM*
*Metropolitan Catholic Archbishop of Addis Abeba*
*President of CBCE & Chancellor of ECU*

This page is sponsored by CAFOD/SCIAF/TROCAIRE

**"When they came into the house, they saw the child with Mary his mother, and they fell down and worshiped him." Matthew 2:11**

# LINK

# የጥሪ ማዕድ

## የሕክምና ተልዕኮ እህቶች ማኅበር
## Medical Mission Sisters

*Called to be a healing presence at the heart of a wounded world*

"ብርሃናችሁ በዓለም ሁሉ ይብራ" ማቴ. 5: 16

"let your light shine" Mt. 5 - 16

ማህበራችን እ.ኤ.አ በ1925 በሲስተር አና ደንግል (ዶር) Sister Anna Dengel (Dr.) በአሜሪካ ተመሠረተ

**የማህበራችን ዋነኛው ዓላማ -** የክርስቶስን የማዳን ሥራ አገልግሎት በሕክምናና በተለያዩ የአገልግሎት ዘርፎች ቀጣይነት እንዲኖረው ማድረግ።

**መስፈርታችን -**

- በቅድሚያ ሕይወቷን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር አገልግሎትና ለድሆች መስጠት የምትፈልግ
- ለጸሎትና ለእግዚአብሔር ትልቅ ስፍራ ያላት
- በዓለም አቀፍ ማኅበር መኖርና ማገልገል የምትፈልግ
- የትምሕረት ደረጃ 10+2 እና ከዚያም በላይ

ቦሌ ጌስት ሃውስ አካባቢ
ቤት ቁጥር - 68
አድራሻችን አዲስ አበባ / ቂርቆስ - ወረዳ 01

የስልክ ቁጥር
0911055968
0911400139
0911106561
0923241466

ፖ.ሣ. ቁጥር 2891

| | |
|---|---|
| አድራሻችን | ወልቂጤ ጉራጌ |
| ስልክ ቁጥር | 011 3 30 52 37 |
| ፖ.ሣ. ቁጥር | ሲስተር ንግሥት ብሩ 11 |

## የኮንሰላታ ማርያም ልዑካን እህቶች እና አባቶች ገዳም

"የኮንሰላታ የአጽናኟቷ ማርያም ልዑካን እህቶች እና አባቶች ገዳም ዓለም አቀፍ ተልዕኮ ያለው ሲሆን የገዳማችን ልዩ ምልክት እግዚአብሔር ኢየሱስን አጽናኝ አድርጎ ለዓለም እንደሰጠ እኛም ለዓለም ሁሉ የምሥራቹን ቃል ማብሰር ነው።"


**"…. ሕዝቤን አጽናኑ አጽናኑ" (ኢሳ. 40 :1)**

እኛ የአጽናኟቷ ማርያም ልዑካን እህቶች እና አባቶች በብፁዕ ዮሴፍ አላማኖ አማካኝነት ቶሪኖ በሚባል በጣሊያን ከተማ ገዳማችን ተመሰረተ።

የተጠራነውም በፍቅር እንድንኖርና በተጠራንበት የፍቅር ሕይወት የእግዚአብሔርን ቃል ላልሰሙት ለማብሰር ነው። ይህንንም የምናደርገው በሕብረት በመኖር፣ ዛሬ በምንገኝባቸው አገሮች፣ በአፍሪቃ፣ በእስያ፣ በአውሮፓ፣ በሰሜንና በደቡብ አሜሪካ ከማህበረሰቡ ጋር በመኖር የተለያየ አገልግሎት በመስጠት ላይ እንገኛለን።

**የገዳማችንን መንፈስ ለመከተልም ሆነ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ፍቅር እና መፅናናት ላልደረሳቸው ለማድረስ ለምትሹ እህቶች/ ወንድሞች ሁሉ -** የገዳማችን መጠይቅ እንደሚከተለው ነው

1. በቅድሚያ ራሷን/ራሱን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር አገልግሎት መስጠት የምትፈልግ/ የሚፈልግ
2. የእግዚአብሔርን ቃል ላልደረሳቸው ማብሰርና የተልኮ ሕይወት ለመኖር ሙሉ ፍላጎት ያላት/ ያለው
3. 10+3 ወይም ዲፕሎማ 12+3 Degree (ዲግሪ) ከዛም በላይ በማንኛውም ዘርፍ የትምሕረት ማስረጃ ያላት/ ያለው
4. ለአባቶች 12ኛ ክፍል ይቀበላሉ



Our Lady of Consolata
Pray for Us

**"ታላቅነቴን በሕዝቦች መካከል ያውጃሉ" (ኢሳ. 66 :18)**

ስልክ
**0912-14-26-37**
**011-3-21-01-47 / 48**

የፖ.ሳ ቁጥር
**145069 / 22748**

አድራሻ
**ኮንሰላታ ሲስተሮች/ አባቶች አዲስ አበባ መካኒሳ ከመካነየሱስ ሴሚናሪ ፊት ለፊት**

## በአዲስ አበባ ካቶሊክ ሃገረስብከት ሴቶች ዕድገት ቴክኒክና ሙያ ትምሕረትና ስልጠና ማዕከል

(ካሀሴዕማ/ቴ/ሙ/ት/ስ) አ.አ.

**Catholic Archdiocese Women's Promotion Technical and Vocational Education & Training Center**

(CAWPC / TVET) A. A

**" Come and see us. You will be most welcome! WE ARE WAITING FOR YOU! "**

በዝቅተኛ የኢኮኖሚ ደረጃ ላይ የሚገኙና የቀለም ትምህርታቸውን በተለያዩ ምክንያቶች አቋርጠው የሙያ ስልጠና ፍላጎት ያላቸውን ወጣቶች ለማገዝ በአነስተኛ ክፍያ የስልጠና አገልግሎት በማግኘት ለሥራ ብቁ የሚያደርጉና ለገቢ ማስገኛ እንቅስቃሴ የሚያዘጋጁ የሙያ ስልጠናዎችን በመስጠት ላይ እንገኛለን።

**በአጫጭር ስልጠና**
**(Short training)**
በደረጃ አንድና በደረጃ ሁለት
Level (1) one and Level (2) two

**የሚሰጡ ስልጠናዎች**

1. ልብስ ቅድና ስፌት
2. ህትመትና ማቅለም
3. የተሻሻለ የሸመና ሥራ
4. ጥልፍ በእጅና በስፌት መኪና
5. ሹራብ በእጅና በማሽን
6. ምግብ ዝግጅትና መስተንግዶ

ሀ - ከ 3-6 ወራት አጭር ኮርስና
ለ - ለ 10 ወራት በመረጡት ሙያ ስልጥነው እራስዎን ለሥራ ያዘጋጁ።

**በማዕከአችን የስልጠና አገልግሎቱ ቀጣይነት በጥራት የሚያመርታቸውን የዕደጥበብ ምርቶች በተመጣጣኝ ዋጋ በመግዛት ተጠቃሚ እንዲሆኑ እንጋብዛልን።**

**አድራሻችን**
አራዳ ክ/ከ ፒያሳ
ካቶሊክ ካቴደራል ት/ቤት
ቅጥር ግቢ ውስጥ

**ስልክ ቁጥር**
011 111 4786 / 011 157 5927

**E-mail**
cawpc@ethionet.et









**ስለ"ፍቅርና ሰላም ጋዜጣ" አስተያየት ካለዎት በስልክ ቁ. (0111) 55 03 00 በመደወል ለፍቅርና ሰላም ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ያካፍሉን!**



**ወንጌልን በጋራ እንስበክ**

**ሌሎች ቢያነቡዋቸው ትምሕረት ያገኙባቸዋል ብለው የሚያምኑባቸውን መጣጥፎች እና የወንጌል አስትምህሮዎች ይላኩልን**

ፖ. ሣ. ቁ. 2454 አዲስ አበባ ስልክ - (0111) 55 03 00 ፋክስ (0111) 55 31 13 E-Mail - scpr@eccsdco.org